50 Lonsdale Street,
Melbourne Victoria 3000
GPO Box 4057, Melbourne Victoria 3001
DX 210081

**OFFICIAL**

ነዋሪ
259 ማልቨርን ሮድ
ሳውዝ ያራ

ውድ ነዋሪ

ሆምስ ቪክቶሪያ ስለ ታላቁ የቤቶች ግንባታ ሂደት እና ስለ ሰማይ-ጠቀስ ፎቆች የመልሶ ማልማት መርሃ ግብር እድገት ለማሳወቅ ነው የሚጽፈው።

የፕሮግራሙ ቀጣይ ምዕራፍ አሁን በ 7 አዳዲስ ቦታዎች በመካሄድ ላይ ነው። ይህ ማለት አሁን በ9 መንደሮች ወይ ሰበርቦች ለሚኖሩ የአሁኑ እና የወደፊት ነዋሪዎች የተሻሉ፣ ደህንነታቸው የተጠበቀ እና ምቹ የሆኑ ቤቶች ወደ ማቅረቡ እያመራን ነው።

## ዛሬ ይፋ የተደረገው ምንድን ነው?

ዛሬ፣ እነዚህን ሕንፃዎች እንደገና ስለማልማት ከነዋሪዎች ጋር ተነጋግረናል፦

- 25 እና 27 ኪንግ ስትሪት፣ ፕራሃን
- 150 ቪክቶሪያ አቬኑ፣ አልበርት ፓርክ
- 150 ኢንከርማን ስትሪት፣ ሴይንት ኪልዳ
- 159 ሜልሮዝ ስትሪት፣ ኖርዝ ሜልበርን
- 29 ክራውን ስትሪት፣ ፍሌሚንግተን
- 94 ኦርመንድ ስትሪት፣ ኬንሲንግተን

በእነዚህ የሰማይ-ጠቀስ ፎቆች ሕንፃዎች ውስጥ ከሚኖሩ ነዋሪዎች ጋር በመደበኛነት እንገናኛለን። **ከጁላይ 2026 እስከ ፌብሩዋሪ 2028፣** ብዙ እና የተሻሉ ቤቶችን በምናቀርብበት ጊዜ ወደ ተስማሚ ቤት እንዲዛወሩ ለመርዳት ከእነዚህ ቤተሰቦች ጋር በቅርበት እንሰራለን።

## የመዛወር እቅድዎን መደገፍ

በ259 ማልቨርን ሮድ፣ ሳውዝ ያራ የቀሩትን ነዋሪዎች ወደ ሌላ ቦታ እንዲዛወሩ መደገፋችንን እንቀጥላለን።

ከ90% በላይ የሚሆኑ አባወራዎች ተዛውረዋል፣ ወይም በመዛወር ላይ ናቸው፣ እና ሁሉም እስከ ፈብሩዋሪ 2026 ድረስ ለመዛወር በሂደት ላይ ናቸው።

## በሂደቱ ውስጥ እርስዎን መደገፍ

**ራሱን የቻለ የማዛወር ቡድን አለን** ይህ ቡድን የእርስዎን ፍላጎቶች እና ምርጫዎች ለመረዳት ከነዋሪዎች ጋር በቅርበት ሲሰራ ቆይቷል። ፍላጎቶችዎን የሚያሟላ ቤት እንድናገኝ ለመርዳት ይህ መረጃ አስፈላጊ ነው።

**ከእርስዎ ጋር ለመገናኘት እዚህ መጥተናል፦** ከእኛ ጋር ለሚያደርጉት ማንኛውም ስብሰባ የቤተሰብ አባል፣ ጓደኛ ወይም አማካሪ ማምጣት ይፈልጉ እንደሆነ ሊነግሩን ይችላሉ። አስተርጓሚም ማዘጋጀት እንችላለን ።

**መብቶችዎ ተመሳሳይ እንደሆኑ ይቆያሉ፦** የሚዛወሩበት ቤት በመኖሪያ ተከራዮች ህግ መሰረት ሁሉም ተመሳሳይ መብቶች እና ጥበቃዎች ይኖረዋል።

**እንዲንቀሳቀሱ መርዳት** - ዕቃዎች የሚጭኑ እናዘጋጃለን፣ እንደ ስልክ፣ ኢንተርኔት ማገናኘት እና የፖስታ ማዘዋወር አገልግሎቶችን እናዘጋጃለን፣ እንዲሁም ከጤና እና የድጋፍ አገልግሎቶች ጋር እንዲገናኙ እናደርጋለን።

**ተመልሶ መምጣት፦** ስራው ሲጠናቀቅ ቀጣይነት ባለው ብቁነትዎ፣ ፍላጎቶችዎ እና የአዳዲስ ቤቶች ተስማሚነት ላይ በመመስረት ወደ ሰፈርዎ የመመለስ መብት አለዎት።

## ግንኙነትዎ አያቋርጡ

ስለ መኖሪያ ቤት ፍላጎቶችዎ እና ለቤተሰብዎ ሊስማሙ ስለሚችሉ ሁሉም ቦታዎች ወደ ሌላ ቦታ የመዛወር ኣስተባባሪዎ/መኮንንዎ ጋር እንዲነጋገሩ እናበረታታዎታለን።

የመዛወር ኣስተባባሪዎን/መኮንንዎን በቀጥታ ማነጋገር ወይም ወደ የማዛወር ቡድን በ relocationsteam@homes.vic.gov.au ኢሜይል ማድረግ ይችላሉ።

## ለተጨማሪ መረጃ

- homes.vic.gov.au ን ይጎብኙ
- ከአካባቢዎ የቤቶች ቢሮ ጋር ይነጋገሩ
- ለዚህ ጉዳይ ወደተዘጋጀው የድጋፍ መስመር በ 1800 716 866 ይደውሉ

ከሰላምታ ጋር

**Simon Newport**
ዋና ሥራ አስፈፃሚ
ሆምስ ቪክቶሪያ

28/01/2026